# ሠ ቅ ጸ ል

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፫ ቀን: ጥር ፫ቀን፪ሺ፲ዓም

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ




## የታሪክ ሽሚያ! ታጥቦ ጭቃ!

ዘመናዊው የፖለቲካ ትውልድ ብለን ልንጠራው የምንችለው የኛው ትውልድ፣ የፖለቲካ ዕድሜው ከ60 ዓመታት አያልፍም። ከተግባራዊ እርምጃው ዘንድ እንነሳ ካልን ደግሞ፣ በእርግጠኝነት ከታህሳስ 1953 ዓም በትውልዱ የተወሰደው የመፈንቅለ ንግሥና እርምጃው ዘንድ ይጀምራል። በብዙው የትውልዱ ምሑራን ዘንድ የወታደሩን ክፍል እንቅስቃሴ የትውልዱ አካል አድርጎ ያለመመልከት አባዜ እንዳለ እግረመንገዳችንንም መጥቀስ ተገቢ ይሆናል።

ይህ የኛው የፖለቲካ ትውልድ፣ ከበስተኋላው የነበር ቅርሱ የሚያወላዳ አለመሆን፣ ለዛሬው አካሄዳችን ዛሬም ከፍተኛውን ሚና ሲጫወት እንመለከታለን። ከየት ጀመረ የሚለውን ለመዳሰስ ትንሽ ወደኋላ መመልከት የግድ ይላል። ከኛ በስተኋላ የነበረውን ጠመዝማዛውን ታሪክ ስንመለከት እኛን ወደፊት የሚገፋ አልነበርም። የመዘመን ትግሉ የተጀመረው ከዐደዋ ድል በኋላ ወዴት ነው አቅጣጫችን ከሚለው ጥያቄ ተነሳ። ለዚህ ሀሳብ መነሳት ያደረሰው የውጭ ወረራ ሥጋትና የኤርትራ በአቅኚው እጅ መቆየት፣ ለእንደገና ጦርነት አይቀሬነት ፍንትው ብሎ መታየት ነበር። በዚህ ምን ይድረግ? ዙሪያ ሁለት ክርክሮች ተነሱ። አንዱ በንጉሠ ነገሥቱ አመለካከት ዙሪያ በቆሙ ተራማጅ አሳቢዎችና በሌላው ጎን በእቴጌይቱና በቤተክህነት ዙሪያ በቆሙት መሀል የተንጸባረቀው ልዩነት ነበር። በንጉሡ አመለካከት የነበረው አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ቶሎ ካልዘመነች በሥልጣኔ እየታገዘ የሚመጣውን የአቅኚዎችን በትር መቋቋም አይቻልም የሚል ነበር። በተቃራኒው በእቴጌቱ፣ በቤተክህነትና ባላባቶች በኩል የተያዘው አቋም፣ የውጪ ኃይል ዋና የመግቢያ በር፣ከውጪ የሚገባ ሥልጣኔ ይዞት የሚመጣው መዘዝ ነው የሚል ነበር። ይህ ትግል ለትውልድ አልፎ በተከተለው ትውልድ በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንንና በንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና በደጋፊዎቻቸው መሀል ተመሳሳይ ትግል ተካሂዶበታል።

በኃይለሥላሴ አገር የማዘመን ሂደት ከኋላቸው ቁመው የነበሩት የዘመኑ አንጋፋ ምሑራን እንደ ነጋድራስ ገብረሕይዎት ባይከዳኝ፣ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረ-የሱስ፣ አለቃ ታዬንና የመሳሰሉት ከምዕራቡ ሥልጣኔ ይልቅ ከባህልና ከንጉሣዊ አስተዳዳር ተመሳሳይነት አኳያ ከጃፓን ሥልጣኔ ጋር መቀራረቡን መረጡ። በዚያም መሠረት ከጃፓን ጋር ግንኙነቱ እንዲመሠረት ሆነ። ከዚህ ግንኙነትም ጋር የምዕራብ የተጠቃለለ የፀረ-ኢትዮጵያ የጥላቻ ዘመቻ ተጀመረ። ለዚህ ዘመቻ ግንባር ቀደሙን ሚና የተጫወተው በ1927ዓም ሮማን ፕሮሽዝካ የተባለ የአውስትሪያ ተወላጅና የናዚ ተከታይ የተጻፈ የፕሮፓጋንዳ መጽሐፍ አንዱና ዋናው ነበር። የመጽሐፉ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያን በኢጣልያን ማስወረር ነበር። ዋና ማቀንቀኛውም ያተኮረው የኢትዮጵያን በነፃነት ወዳጅ የመምረጥ መመሪያ በምዕራባውያን ላይ የዐማራውን ንጉሥ በማወቅ የተሰነዛረ ፖሊሲ መስሎ እንዲቀርብ ማድረግ ነበር። ክሱም «አብሲኒያ ጥቁር አደጋ » በሚል መፈክር ባሸበረቀ የሞሶሎኒ ፕሮፓጋንዳ ዙሪያ ከሩቅ ምሥራቅ ፀረ-ነጭ ከሆነ ጃፓን ጋር ግንባር ፈጥሯል የሚል ክስ ነበር። በወቅቱ ሞሶሎኒ ለወረራው ከፍተኛ አጋር የማሰባሰብ ጥረቱ ይህ ፕሮፓጋንዳ ከፍተኛውን ሚናን ተጫወተለት። የሮማን ፕሮችዝካ ሀሳብ በአውሮፓውያን ወራሪዎች ጎሊና ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በኛ የፖለቲካ ትውልድም ውስጥ ባሉ የባንዳ ባንዶችና ተገንጣዮች ጎሊና ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ይዞ፤ ለዛሬው ትውልድ ዋና የፖለቲካ ትንቅንቃችን መሠረት ሆኗል። **የሮማን ፕሮችዝካ ኢትዮጵያን ከውስጥ የመበተን ዕቅድ የሆነው የፀረ-ዐማራና የፀረ-ኦርቶዶክስ እምነት የመታገያ መመሪያቸው ሆነ።**

ታሪክ እንደ ልጓም ይጠቅሳል ነውና፣ ዛሬ ፀረ-ዐማራና በፀረ-ኦርቶዶክስ ዙሪያ የተሰባሰበ ሁሉ መነሻ መዝገቡ ከኢጣሊያን የካቶሊክ የባንዳ፣ ከጀርመን የፕሮቴስታንት እምነት ወረራና ተጽዕኖ ዘንድ መሆኑ አሌ አይባልም። የዛሬን የፖለቲካ ምህዳሩን አጣቦት ያለ ይህ ውጪ አደር ኃይል መሆኑም የሚታይ ነው። ይህ ከበስተኋላው ምንም የመቻቻልና የመደማመጥ፣ ልዩነቶችን በውይይት የመፍታት የፖለቲካ ውርስ አልባው፣ በሃምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ የተነሳው ትውልድ ወደቀኝና ወደግራ እየተላተመ ከቀኝ የፕሮችስዝካን አስተምህሮ ሲገለብጥና መመሪያው ሲያደርግ፣ ወደግራ ሲገለበጥ ከቀኙ መምህር አስተምህሮት ጋር ተጋበኦ አለው ብሎ ያመነውን የስታሊንን የግራ የብሔረሰብ መመሪያ እንዳለ ሲገለብጥና ሁለቱን ሲያዳብል መምጣቱ ያየነው እውነት ነው። ማየት ብቻም አይደለም። ሄራው ፍሬ አፍርቶ ኤርትራ የተባለች ሀገር እንድትመሠረት አድርጓል። የትግሬ ግዛትም በሂደት ላይ መሆኑ የሚታይ ነው። የኤርትራውና የትግሬው የፕሮችዝካ ንድፈ ሀሳብ ደቀመዘምራን በዐማራና በኦርቶዶክስ እምነት ላይ ልዩ፣ ገና ያላለቀና በሂደት ዝግመታዊ የሆነ የዘር ማጥፋት ዘመቻቸውን ለማጠናቀቅ የማይረዱት አድርባይና የተገንጣይ ኃይል የለም። ይህ ዘመቻ ላለፉት 60 ዓመታት የተካሄደ የረቀቀና እንዳይታይ፣ እንዳይታሰብና እንዳይነቃበት ሁኖ የተሠራ መሆኑም የሚታይ ነው። ዛሬ ዐማራው እልቂት አንገሽግሾት፣ ያለው ብቸኛ አማራጭ ፣ ተደራጅቶ መታገል ብቻ መሆኑን ተገንዝቦ ሲነሳ፣ እነዚያው ደመኛ ጠላቶቹና በጎብረ-ብሔር ስም ተደራጀን ተብዬ አድርባይ ኃይሎች፣ ዐማራ የሚደራጀው ቀድሞ ያጣውን ሥልጣኑን ለማስመለስ ነው፤ ካልተሳካለትም ሊገነጠል ነው፤ በሚል ማወናበጃ ዋናውን የነገዱን የተከላከሎ ዘመቻውን እውነት ሊደብቁ ሲጥሩ ይታያሉ። በነሱ እምነት የዐማራ እልቂት የሚባል የለም። እናም በዚህ ረገድ ከባለ ፕሮግራሙ የትግሬ-ወያኔ አልፈው በመሄድ እሱ ያልካደውን፣ በገሐድ ያለውን፣ ባይን የሚታየውንና በዕቅድ የሚካሄደውን የዘር ፍጅት ሊክዱ ይዳዳቸዋል። እነሱንም በእልቂት ፕሮግራሙ አመራር ሰጪው ወያኔ ግን፣ አልካደም።

# የታሪክ ሽሚያ! ታጥቦ ጭቃ! መቅደላ

እናም ዘመቻቸው የዐማራን የኅልውና ትግል ለማግለል፣ ለመነጠልና በጠላት ለማስመታት የማይወጠን ሤራ፣ የማይገነባ ግንባርና የማይደረግ የታሪክ ሽሚያ የለም። **ታጥቦ ጭቃ ያለው ይህን ታዝበን ነው።**

ይህ ታጥቦ ጭቃነት፣ የዚህ ትውልድ የ60ዓመት ታሪክ ነው። በንጉሡ ላይ ምድር አንቀጥቅጥ የሕዝብ ኃይል ሲነሳ ተደራጀሁ ባለው ትውልድ መሀል የተነሳ መሠረታዊ ልዩነት አልነበርም። ከፊውዳሉ በቀር የመሬት ላራሹን ጥያቄ የተቃወመ ድርጅት አልነበረም። በሀሰት በተፈበረከው "የብሄረሰብ ጥያቄ" የሚያራርቅ ልዩነት አልነበረም። በአስተዳደሩ የሽግግር ጊዜ ጠባይ ልዩነት አልነበረም። የነበረውና ያባላው ልዩነት ማን ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ሥልጣን የሚያስገኘውን እፍታ ይዛቅ? የሚለው ብቻ ነበር። ስለዚህ ይህንን ቦታ ተወዳድሮ ማግኘት የሚቻል በጠመንጃ ነበርና፣ ባለጠመንጃው ደርግ ወሰደ። ውድድሩ የሥልጣን ባለቤቱን ሕዝብን አስቀምጦ የተደረገ የምሑራን ነን ባዮች የታሪክ ሽሚያ ነብር። በዚህ የታሪክ ሽሚያ በረድፍ የቆሙት እንዳለ ጠፍተው ሀገሪቷንም አጠፏት ።

ይህ ከሆነ ዛሬ 46 ዓመታት አልፏል። ከዚያ ቀጥሎ የመጣው፡የዛሬው የፖለቲካ ትውልድ፣ ከዚያ የታሪክ ሽሚያ የታጥቦ ጭቃ የጥፋት ጎዳና አልወጣም። ዛሬም ይህንን የጥፋት፣ የእኔ ካልመራሁት አባዜ ሊተው አልቻለም። እሱ የሚፈልገውን ለማግኘት ሲል፣ እራሱን እንደ ብቸኛ አማራጭ በመቁጠር ለነጭው ዓለም እራሱን ያስተዋውቃል። ከፈረሱ ጋሪው እንዲሉ ጉዳዩን ካገሩ ልጅ፣ ከሚመለከተው ጋር ቀድሞ መክሮ ተወያይቶ መራመድ የሚባለውን ከአፍና ከድለላ ባለፈ በተግባር የሚያደርገው እውነት የለም።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በዛሬው የሀገራችን ጉዳይ ላይና በተለይም በዚህ ወሳኝ የሞት የሽረት ትግል ውስጥ ሁነን የሚነሳ ማንኛውንም ሀገራዊ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሁሉ ተካቶ ሳይመከረበት የሚወሰድ እርምጃ የስልሳዎቹን አስከፊ የድርጅቶችን መተላለቅ ታሪክ መድገም ይሆናል ብሎ ያምናል። ልብ ያለው ልብ ይበል። በ60ዎቹ ይህ እኔነኝ ባይነት ነው እፊታችን አድኅና አፈርቶ የአምባገነንነትን አዝመራ እንድናጭድ ያደረገን። በሂደትም ለሀገራችን መከፋፈል መነገዱን የጠረገና ለኤርትራም መለየትና ለዛሬ ውድቀታችን የዳረገን። ዛሬም አንዳንድ እኛ ነን ባዮችን ልጓማቸውን ለማጥበቅ ካልተቻለ ፣ እነሱ በሚጭሩት የታሪክ ሽሚያ ታኮ በሚመጣ ብጥብጥ ባለተራ ነን ብለው ባደባባይ የሚዶሶኩሩና በተግባርም እየሠሩ ላሉ ተገንጣዮች በሩን መክፈት ይሆናል።

ለመገንባት ካልሆነ በቀር፣ ለጥፋት ማንም ከማንም አያንስም ። ኢትዮጵያ ደግሞ ለዚህ የታደለች ነች። ይህ የኛው ታሪክ ነው። የድርጅታችን ጥሪ ቀላሉን የመጠፋፋቱን ጎዳና ትተን፣ ከባዱን ግን አልሚ የሆነውን ሁሉንም ዜጎቿን ወደሚያካትት ፖለቲክ እንግባ የሚል ነው። ያለፈው የ60ዓመታት የኔ መንገድ ብቻ፣ የጥፋት ጎዳና እንደማያዋጣ እንዴት ማየት ይሳነናል? ብለን እንጠይቃለን። ከምሑር እኔ ነኝ ባይነት ወደ እኛነት ፖለቲካ እንመለስ። በጋራ እንምከር። በጋራ ተራምደን ሕዝቡ ፊት ቁመን የሱ ውሳኔ እንቀበል። ዛሬ ብዙ አንገብጋቤ ጉዳዮች ከኛ መልስ ለመሻት ከፊታችን ቁመዋል።

ከነዚህም ውስጥ የጋራ ጠላት ወያኔን በጋር እንዴት እንታገለው? የጋራ በሆኑ ጉዳዮቻችን ዙሪያ እንዴት አብረን እንቁም? ከድሉስ በኋላ ያለውን የሽግግር ጊዜ ካለፍነው የሽግግር ተሞክሮ በተለየ መንገድ ሕዝብ አሳታፊ የሆነ የሽግግር ዘመን እንዲሆና ምን መደረግ አለበት? ከሽግግር ዘመኑ በኋላ ያለው ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ምን ይመስላል? ወዘተ የሚሉት ለብቻ እያንዳንዱ ድርጅት ሕልሙን በመያዝ ባንድ ላይ የውይይት መድርክ በመክፈት የሁሉ የሆነ ሰነድ ማዘጋጀት ይገባል እንላለን፡፤ ከዚህ የወጣ አካሄድና የኔ ነው የሁሉ የሚለውና ከቤት አወጥቶ ለዓለም አደባባይ ቀድሞ እንዲታወቅ የማድረግ አባዜ ትናንት የመጣንበት የጥፋት የታሪክ ሽሚያ አካሄድ ነው። ይህ ሲያልፍ ለተከተሉት እንዳላዋጣ ሁሉ ለዛሬዎቹ ተከታዮቻቸውም አያዋጣም። እኛን የሚጨንቀን የነሱ እጣ ፈንታ ሳይሆን፣ እኛን የሚጨንቀን በነዚህ የነገ እጩ አምባገነኖች ጥላ ሥር አድብቶ ለመገንጠል በመሥራት ላይ ያለ ኃይል ሊያስከትል የሚችለው ጥፋት ነው። ባሳዛኝ ሁኔታ ታሪክ እራሷን እንዳትደግምብን እንፈራለን። ለዚህም ነው ይህንን አካሄድ የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መላው ሕዝባችንና ለሀገራችን ቅን የሚያስብ ዜጋ ሁሉ የዚህን የጥፋት ሂደት በትኩረት እንዲከታተለው ጥሪውን የሚያስተላልፈው።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በሽግግሩ ወቅት ሕዝባችንን ያቀፈና ወሳኙን ሚና ተጫዋቹም ሕዛባችን መሆኑን በሚያረጋግጥ መልኩ ያዘጋጀውን ሰነድ በቅርብ ለሕዝባችን ለውይይት ያቀርባል። ሌሎችም ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ድርጅቶችና ስብስቦች የየራሳቸውን ሰነድ በማዘጋጀት ለሕዝባቸው ለውይይት ቢያቀርቡ ድርጅታችን የሚደግፈው ነው። የሕዝባችንን የበላይነት እስካልተጋፉ ድረስ የሁሉም ባንድ ላይ ተጋብቶና ዳብሮ ሀገራዊ የሽግግር ጊዜ ሰንድ እንዲወጣው ድርጅታችን ይሠራል። በዚህ ረገድ ከዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጋር ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ከሚፈልግ ስብስብ ጋር ለመቀናጀት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ኅብረት ከወደቀችበት ትነሳለች!

ውድ እናት ሀገር ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!